# እናንተም ቅመሱ !!

ከአቤ ኮስትሬ

እናንተ ኃያላን በድኃው ከብራችሁ
የላብ የደሙን ወዝ በግፍ መጥምጣችሁ
ድኃው ላይ ነግሣችሁ !
ሰብዓዊ ክብሩንም እጅግ ዝቅ አርጋችሁ !
በፈላጭ ቆራጩ እኩይ ሥልጣናችሁ
አሰቃያችሁት በትዕቢት ረግጣችሁ !
ከሕዝብ አብልጣችሁ አንዱን ዲክታተር
በደም ስትጨቀይ ተንገፍግፋ ምድር
የዘገየ ቢመስል አይመጣም ብላችሁ
ዕንባ አባሹ ጌታ ቆሟል ከደጃችሁ !

በውሸት ዲሞክራሲ ታፍነን ስንቃትት
ሰላም ነፃነትን ለማግኘት ስንዋትት
ፍርድ ተጓድሎብን ድምፃችን ሲቀማ
ከሕግ ሳንወጣ ጩኸት ብናሰማ
እናንተው ነጥቃችሁ !
እናንተው ዘርፋችሁ !
እናንተው አሥራችሁ
እናንተው ገድላችሁ !
ዲሞክራሲ ሳይኖር ያለ አስመስላችሁ !
ያለምንም ዕፍረት ሕዝብን ጨፍጭፋችሁ
አሁንስ አይበቃም ስንነቃባችሁ ?

ጎምዝዞ ቢመረን ቢያቅለሸልሸን
ሁሉን ቀምሰነዋል ጊዜ የቸረንን !!
እናንተም ቅመሱ የጊዜን ችሮታ
ቢመር ቢጎመዝዝ ነውና ግዴታ !
በኛ ችግር ሥቃይ ደስታ ተሰምቷችሁ
ለደስታው መግለጫ ሻማ ሳበራችሁ
ለናንተም ሲመጣ መዓተ-ቅሥፈቱ
ዝግጁ ነን እኛም ሻማ ለማብራቱ !

በጦርነት እሳት ስታቃጥሉን
በኢኮኖሚ ቀውስ ስታዳሽቁን
በረሃብ ቸነፈር ስትገነትሩን
በመርገምተ-ስደት ስታባዝኑን
በማዕቀብ አሥራችሁ ስታሠቃዩን
ብሶት ብንናገር ሰሚ ጆሮ አጥተን !
እየመጣኮ ነው ዕውነተኛው ዳኛ
ድሆቹን ሊረዳ ሊየጠፋ ዕብሪተኛ
ሥራውን ጀምሯል አይተናል በገሃድ
ከክፋት ታቀቡ ኃይላችሁ ሳይናድ ፤

እኔኮ ብቻ ነኝ አልፋና ዖሜጋ !
ለሁሉ የእጅ ሥራ የምከፍል ዋጋ
ከኔና ከናንተ የሚያሸንፍ ማነው ?
እናንተ በብረት እኔ በውሃ ነው !
በብረትም ቢሆን የኔ ይጠነክራል !
ቁጣዬን ስልከው የናንተው ይቀልጣል !
በልበ-ትዕቢት ትዕዛዜን ጥሳችሁ !
ድሃዎች ሕዝቦቼን በመጨፍጨፋችሁ !
ሀብተ-ቅርሳቸውን በመበዝበዛችሁ !
በጦርና ጎማም በማስጨነቃችሁ !
ጠርቶኛል ከሰማይ የንጹሃን ደም !
ሳልበቀላችሁ ጨርሶ አልቀርም !!

መምጫዬን አታውቁም ደቂቃ ሰዓቱን !
የመቅሠፍቴን ዓይነት በራድ ትኩሳቱን !
ሳይክሎንም ይሁን መሬት ማንቀጥቀጡን
በጎርፍ ማጥለቅለቁን በእሳት ማጋየቱን !
ምን ብትመረምሩ ብትፈላሰፉ
መምጫዬን ሳታውቁ በከንቱ እንዳትለፉ
እንግዲህ መጣሁኝ ኃይላችሁን ላየው
እሳት ውሃ ቀስቴን ማነው የሚቋቋመው ?
ማነው ከናንተ ውስጥ እሳት የማይፈራ ?
መቅጫ ያደረግሁትን ለሰዶም ገሞራ !
በዘመነ ኖኅስ ውሃዬን ማን ቻለው ?
ሕይወቱን ከጥፋት ያዳነው ሰው ማነው ?
ቀስቴን ገትሬያለሁ ውሃው ተሰናድቷል
አውሎው ሊወነጭፍ ነፋስ አጉረምርሟል
አይችልም ለማዳን ልበ-ትዕቢታችሁ
የት ነው መደበቂያው ዋሻው መሸሻችሁ ?
ብርና ወርቃችሁ ዕንቁው አልማዛችሁ
በብረት በድንጋይ የገነባችሁት
ጠንካራ ዋሻችሁ አለኝታ የምትሉት
አያድናችሁም ከልብ አስተውሉት !
ቢገባ ይግባችሁ ባይገባችሁ ተዉት
መቅሠፍቴ ይወገድ ወይም ተቀበሉት
በቅድመ ነቢያት ተናግሯል ጌታችን
እንኑር ተዛዝነን ይጥፉ ቅራኔያችን !

እግዚአብሔር በውሃ እናንተ በብረት
ከቶ አትመጥኑትም የላችሁም ጉልበት
በእሳት በነፋስም ቢጨመድዳችሁ
ከልቅሶ በስተቀር ምን አቅም አላችሁ ?
ገና ካልገባችሁ የትዕግሥት ውጤቱ
የአልፋና-ዖሜጋ  መዓተ-ቅሥፈቱ
ብዙ ጉድ ይኖራል ቆሟል ከፊታችሁ
የእጃችሁን ዋጋ ትቀበላላችሁ !
በኛ ችግር ሥቃይ ደስታ ተሰምቷችሁ
ለደስታው መግለጫ ሻማ ላበራችሁ
ለናንተም ለይቶ ሲመጣ ቅሥፈቱ
ዝግጁ ነን እኛም ሻማ ለማብራቱ !
ከሕዝብ አብልጣችሁ አንዱን ዲክታተር
በደምና እንባ ተጨማልቃ ምድር
ይህን ገደብ አልባ ግፈኛ ሥርዓት
ለናንተ ኢንተረስት ብትደጋግፉት
ልታዘቀዝቅ ነው ልትጠልቅ ጀንበሯ !
ለድሆች ምሥራች አይቀርም ማብሠሯ !!